Seattle Public Utilities

# 2018-19 አብዛኛውን ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
# የ"ዌስት ፍሪ" ማህበረሰብ ወጪ መጋራት

## የተሻሻለውን በየግዘው የሚጠየቁትን ጥያቄዎች ለማግኘት እባከዎትን ተመልሰው ይምጡ፡፡

**1. የመንግስት ወኪሎች ማመልከት ይችላሉ?**

አይችሉም፣ የመንግስት ወኪሎች  አይፈቀድላቸውም፡፡

**2. ንግዴ/ድርጅቴ ያለው ከሲያትል ክልል ውጪ ነው፡፡ ማመልከት እችላሎው?**

አዎን ይህም ፕሮጀክትዎ በሲያትል ውስጥ የሚደረግ እንደሆነ ወይም የሲያትልን የፍሳሽ ሂደት ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ እንደሆነ ነው፡፡

**3. ከሲያትል ውጪ የሆኑ አካባቢዎችን ወይ ፕሮጀክቶች ላይ ተጽእኖ ለሚያደርጉ ፕሮጀክቶች የግራንት ፈንድን ልንጠቀም እንችላለን?**

ፕሮጀክቶች በዋናነት በሲያትል ላይ ሊያተኩሩ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን፣ አንዳንድ ድርጅቶች የሲያትል ደንበኞቻቸውን ከሌሎች ኪንግ ወረዳ ውስጥ ካሉ ደንበኞቻቸው ለይተው ለማየት ሊቸግራቸው እንደሚችል እናውቃለን፡፡ ከሲያትል ውጪ ለሆኑ ድርጅቶች እንደየሁኔታው አነስተኛ የሆነ ድጎማ ሊደረግ ይችላል፡፡

**4. ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶች የሲያትል ከተማ የንግድ ፍቃድ ያስፈልጋቸዋል?**

በሲያትል ውስጥ ለትርፋማ ድርጅት ወይም ለትርፍ ለማይሰሩ ድርጅት ገንዘብ ማሰባሰቢያ ካደረጉ፣ የሲያትል ከተማ የንግድ ፍቃድ ያስፈልጎዎታል፡፡

**5. የንግድ ፍቃድ ለማውጣት ምንያህል ያስወጣል?**

የሲያትል ከተማ የንግድ ፍቃድ ተመን እዚህ ይገኛል፡ https://www.seattle.gov/licenses/get-a-business-license/cost-of-a-business-license፡፡

የዋሺንግተን ከተማ የንግድ ፍቃድ ተመን እዚህ ይገኛል፡ http://bls.dor.wa.gov/faqlicense.aspx

**6. በአንድ ጊዜ ከ አንድ በላይ ማመልከቻ ልናስገባ እንችላለን?**

አዎን፣ ከአንድ በላይ ማመልከቻ ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡ በሁለቱም ማመልከቻዎ ላይ ተቀባይነት የሚያገኙ አንደሆነ፣ አንደኛው ብቻ ነው ግራንት ስጦታ/ድጋፍ ሊያገኝ የሚችለው፡፡

**7. በጀቱ ትክክለኛ ቁጥር መሆን አለበት ወይስ ግምት ሊሆን ይችላል?**

በጀቶች በተቻለ መጠን ትክክለኛ መሆን ያስፈልጋቸዋል፡፡ ቆይተው ተጨማሪ ገንዘን ሊቀበሉ ሊጠይቁ አይችሉም፣ ስለዚህ በበጀትዎ ውስጥ ሁሉንም ወጪዎች እንዳካተቱ እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

**8. ለምግብ እና መጠጥ ለአንድ ሰው ከፍተኛ የሚባል መጠን አለ?**

በአጠቃላይ፣ ትልቁ መጠን በሰው $10 እንዲሆን እንመክራለን፣ ነገር ግን እንደሁኔታው የሚለያይ ነው፡፡ "SPU" ትልቅ የሚባለው መጠን ምክንያታዊ እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን  ስጦታ/ድጋፍ  እንዲሰጣቸው ከተመረጡ ፕሮጀክቶች ጋር አንድ ላይ ይሰራል፡፡

**9. ለማበረታቻዎች ከፍተኛ የሚባል መጠን አለ?**

በአጠቃላይ፣ ለማበረታቻ የሚሆነው ትልቅ መጠን $25 እንደሆን እንመክራለን፣ ነገር ግን እንደ ሁኔታው ይለያያል፡፡ "SPU" ትልቅ የሚባለው መጠን ምክንያታዊ እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን ግራንት እንዲሰጣቸው ከተመረጡ ፕሮጀክቶች ጋር አንድ ላይ ይሰራል፡፡

**10. ለፕሮጀክቴ የተለየ መድን ያስፈልገኛል?**

በአጠቃላይ፣ ፕሮጀክቶች የሚከተለውን መድን ማግኘት አለባቸው፡

- $1,000,000 በንግድ አጠቃላይ የተጠያቂነት መድን/ዋስትና
- $1,000,000 የመኪና ተጠያቂነት  መድን/ዋስትና
- የሰራተኞች የማካካሻ ክፍያ መድን/ዋስትና

ተለይተው የሚጠየቁ የመድን አይነቶች እንደየፕሮጀክቱ የሚለያዩ ይሆናል፡፡ "SPU" ለስጦታ/ድጋፍ ከተመረጡ ፕሮጀክቶች ጋር አንድ ላይ የሚሰራ ሲሆን ይህም የመድን ፍላጎታቸውን ለማወቅ ነው፡፡ ከመደበኛ ሽፋኖ በላይ የሆነ መርሃ-ግብር ተኮር ኢንሹራንስ በተፈቀደልዎት በጀት ውስጥ እንዲጠቃለል ስምምነት ላይ ሊደረስ ይችላል፡፡

**11. የማመልከቻውን ምን ያክል ግልባጭ ነው መላክ የሚያስፈልገን?**

አንድ ግልባጭ፡፡ በቀላሉ ሊገለበጡ እና ሊላኩ የሚችሉ ግልባጮችን እንዳስገቡ እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

**12. በማመልከቻችን ውስጥ ምን ደጋፊ ዶሴዎችን ልናካትት ያስፈልጋል?**

ከላሾች ብዙ ድጋፍ ያላቸውን ዶሴዎች ለማንበብ ጊዜ አይኖራቸውም፣ ስለዚህ ምን ምን ማካተት እንዳለብዎ የሚከተለው ይገልጥልዎታል፡፡

| አዎን - ከማመልከቻ ጋር ያካቱ | አይ - ከማመልከቻ ጋር አያካቱ |
|---|---|
| • የዋጋ መጥቀሻዎች እና ሌሎች ለበጀት ድጋፍ የሚያደርጉ ግምቶች<br>• ፕሮጀክትዎን ለማብራራት ድጋፍ የሚያደርጉ ምስሎች፣ ካርታዎች ወይም ሌሎች ዶሴዎች፡፡ | • የድጋፍ ደብዳቤዎች<br>• አመታዊ ሪፖርት<br>• ጋዘጣ<br>• የጋዜጣ ቁርጥራጭ<br>• የድርጅት ኦፕሬሽን በጀት ወይም የፋይናንስ ስቴትመንት |

**13. ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ?**

ፕሮጀክቶች ሙሉ “ፈንድ” የማያገኙበት ሁለት አይነት ሁኔታ አለ፡ 1) በጀትዎ ትክክለኛ የሆነ ወጪ የማያካትት እንደሆነ ወይም 2) የክለሳው ኮሚቴ የበጀት ማስተካከያ ማድረግ የሚያስፈልገው እንደሆነ ይህም ለግራት በተመደበው የ $100,000 ክልል ውስጥ ለማስገባት የሚፈለግ እንደሆነ፡፡ አለዚያ፣ እያንዳንዱን ግራንት ተቀባይ ሙሉ በሙሉ ፈንድ ለማድረግ እንሞክራለን፡፡ ለፕሮጀክትዎ የሚያስፈልግዎትን በጀት ያቅዱ እንዲሁም ሆን ተብሎ ከመጠን በላይ መበጀት የለበትም።

**14. ማመልከቻችን ውድቅ ተደርጓል፡፡ እንደገና ማመልከት እንችላለን?**

አዎን በየአመቱ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ እደገና ለማመልከት የሚያቅዱ እንደሆነ፣ በ wastefreegrants@seattle.gov ላይ እንዲያገኙን እንመክርዎታለን ወይም በ (206) 386-9791 ላይ ደውለውልን እንዴት አድርገው ማመልከቻዎትን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ ሊጠይቁን ይችላሉ፡፡

**15. ፕሮጀክታችንን ለማስቀጠል በየአመቱ ልናመለክት እንችላለን ?**

የግራንት ፈንዶች አንድ ፕሮጀክት *ለማስቀጠል* ሊውሉ አይችሉም፣ ነገር ግን አንድ ፕሮጀክት *ለማስፋፋት* ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ አዲሱ ማመልከቻ ተጨማሪ የተረፈ-ምርት ማስቀነሻ ዘደን ማብራራት ያስፈልጋል፡፡

ፕሮጀክትዎ ከከፍተኛው የ $15,000 በላይ የሚሆን እንደሆነ፣ ፕሮጀክትዎን በተለያዩ አመታት ሊከፋፍሉት ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ ክፍል እንደ አንድ ፕሮጀክት የሚታይ ይሆናል፣ ቢሆንም በሁሉም ፕሮጀክቶች ላይ ፈንድ ያገኛሉ የሚል እርግጠኛነት ሊኖርዎ አይገባም፡፡

**16. ፈንድ የሚደረጉ እንደሆነ፣ በምን ያክል ፍጥነት ነው ገንዘብ የሚከፈለን?**

የ”ግራንት ፈንድ” በመልሶ መክፈል መልክ የሚከፈል ነው፡፡ ወርሀዊ ወይንም በሶስት ወር አንድ ጊዜ የከፈሉትን ክፍያ ማስረጃ ሊያቀርቡልን ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱን ደረሰን ካስገቡ በኋላ በ አራት ሳምንታት ውስጥ ክፍያ ለማግኘት ይጠብቁ፡፡